የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት
THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA
OFFICE OF THE FEDERAL
AUDITOR GENERAL

ፌዋኦ/FAC-F.04.23/3/13
ቀን 21/03/2012

ለክብርት ወ/ሮ ዳግማዊት ሞገስ

የወልድያ ዩኒቨርሲቲ ቦርድ ሰብሳቢ

<u>አዲስ አበባ</u>

ጉዳዩ:- <u>የወልድያ ዩኒቨርሲቲ የ2011 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ውጤትና አስተያየትን ይመለከታል፣</u>

ከላይ በርዕሱ የተጠቀሰውን ኦዲት ውጤትና አስተያየት የያዘ 9 ገጽ የኦዲት ሪፖርት እና 51 ገጽ የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች ከዚህ ደብዳቤ ጋር አያይዘን የላክን መሆኑን እንገልጻለን፡፡

ከሰላምታ ጋር

መይሳ ከበደ
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች ኦዲት
ዳይሬክቶሬት

<u>ግልባጭ፣</u>

- ለወልድያ ዩኒቨርሲቲ
  (ከ 9 ገጽ የኦዲት ሪፖርት፣ 51 ገጽ የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች እና 18 የሂሣብ ሪፖርቶች አባሪ ጋር)
  <u>አዲስ አበባ፣</u>

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የወልድያ ዩኒቨርሲቲ

የ2011 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

የወልድያ ዩኒቨርስቲ የተመደበለትን የመደበኛና የካፒታል ሂሳብ በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፣ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መያዙንና የመንግሥ ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2011 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል።

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የዩኒቨርስቲ ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው።

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን ሲሆን፣ ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው። እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል። ኦዲታችን፡-

- በሂሳብ ሪፖርቶች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ ሪፖርቶችን ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል።

ከዚህም በተጨማሪ የተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይጨምራል።

የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል።

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት ዩኒቨርሲቲው ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች፣ መዛግብት፣ ደጋፊ ማስረጃዎች፣ እንዲሁም በኦዲት ተደራጊው መ/ቤት ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው::

ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው::

የሚከተሉት የወልድያ ዩኒቨርስቲ የሂሳብ ሪፖርቶች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል::

- የገቢ/የዕርዳታ/ የብድር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የዝውውር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የሂሳብ ሚዛን ሙከራ፣

<u>ለኦዲት አስተያየቱ መሠረት የሆኑት ጉዳዮች፣</u>

የዩኒቨርሲቲው የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፣ ደንብና መመሪያን የጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

<u>የገቢ ሂሳብ፣</u>

1. የገንዘብ መቀበያ የገቢ ደረሰኝ በነጠላ ቁጥር 973069 እና 973070 በበራሪው እና በቀሪው የተሰበሰበ ገንዘብ አለመኖሩን ደረሰኙ ቢያሳይም፣ በሂሳብ መዝገብ (TR) በዚሁ ገቢ ደረሰኝ ቁጥር 973069 ብር 100,000.00 እና 973070 ብር 150,000.00 በድምሩ ብር 250,000.00 እንደተሰበሰበ ተመዝግቦ ቢታይም ገንዘቡ ገቢ ስለመደረጉ የሚገልጽ የባንክም ሆነ የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ማስረጃ ሳይኖር ሪፖርት የተደረገ በመሆኑ የገቢውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አልተቻለም::
2. ዩኒቨርሲቲው ለውጭ ሀገር መምህራኖች ከተከፈላቸው ደመወዝ ብር 478,417.35 ላይ በድምሩ ብር 155,446.10 የሥራ ገቢ ግብር ሳይቆረጥ ሙሉ ክፍያ የፈጸመ በመሆኑ

ለመንግሥት ገቢ የሚደረገውን የሥራ ግብር መጠን ዝቅ እንዲል እና እንዳይታወቅ አድርጓል፡፡

3. ዩኒቨርሲቲው ከሚፈጽመው ክፍያ ላይ በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 አንቀጽ 92 ንዑስ አንቀጽ 4 መሠረት ከሚፈጽመው ክፍያ ላይ ሰላሳ በመቶ (30%) የገቢ ግብር መቀነስ ሲገባው ቅድመ ታክስ ሁለት በመቶ (2%) ብቻ በመቀነሱ መንግስት ሊያገኝ የሚገባውን ብር 75,682.88 ሳይቀነስ በብልጫ የከፈላቸው በመሆኑ ድንብና መመሪያን ካለመከተሉ በተጨማሪ የመንግሥትን የገቢ ግብር እንዲያጣ አድርጓል፡፡
4. ለምግብ አገልግሎት የሚውሉ ግብአቶች ከሚያቀርበው ድርጅት በውሉ መሰረት እንዲያቀርብ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ የተሰጣቸው ቢሆንም ሊያቀርቡ ባለመቻላቸው በገባው ውል መሰረት ዩኒቨርስቲው ለደረሰበት የስራ መስተጓጎል የጠቅላላ ውሉን 10% ዋስትና ከወሰደው ከወልድያ ከተማ አስተዳደር ቴክኒክ ሙያ ኢንተርፕራይዞች ልማት ፅ/ቤት ብር 502,944.50 (5,029,455.00*10%) የውል ማስከበሪያ ገቢ ያላደረገ በመሆኑ ደንብና መመሪያ ተፈፃሚ እንዳይሆን ከማድረጉ በተጨማሪ ለመንግሥት ገቢ መደረግ የነበረበትን ሂሳብ እንዳይገኝ አድርጓል፡፡
5. ዩኒቨርስቲው በድምሩ የብር 1,645,540.16 የውስጥ ገቢ ሠነዶች ለኦዲት ሥራ እንዲቀርቡ ተጠይቆ ሊያቀርብ ያልቻለ በመሆኑ የገቢውን ሂሳብ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

<u>የወጪ ሂሳብ፣</u>

6. የውሎ አበል ክፍያ ደንብና መመሪያን መሰረት በማድረግ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣
   - ዩኒቨርሲቲው ለአራት ሠራተኞች የቀን ውሎ አበል ክፍያ መቆጣጠሪያና የስራ ክንውን የሚያሳይ የውሎ አበል ማወራረጃ ቅፅ-2 በመሙላት የስራ መግለጫ ያልቀረበ በመሆኑ በተሰብሳቢ መያዝ ሲገባው፣ በድምሩ ብር 8,518.00 በቀጥታ በወጪ የተመዘገበ መሆኑን እና ለሌሎች አራት ሠራተኞች ደግሞ የውሎ አበል መጠየቂያና መፍቀጃ ቅፅ(ቅፅ-1) እና የውሎ አበል ክፍያ ማወራረጃ ቅፅ (ቅፅ-2) አግባብ ባላቸው ሠራተኞች ወይም ኃላፊዎች ሳይሞላ ለሠራተኞችም የተሰጠ የሥራ ስምሪት ስለመኖሩ ምንም ማስረጃ ሳይቀርብ በድምሩ ብር 2,704.75 የአበል ክፍያ የፈፀመ መሆኑን፣

- ዩኒቨርሲቲው ለ9 ሰራተኞች የቁርስና ምሳ አበል ክፍያ ሲከፈል ስራው በተሰራበት ቦታ በመርሳ የአበል ሂሳብ (በብር 112.00) መከፈል ሲገባው በወልድያ አበል በብር 192.00 ሂሳብ እየታሰበ ክፍያ የተፈፀመ በመሆኑ በድምሩ ብር 5,739.80 ያለአግባብ በብልጫ ክፍያ የተፈፀመ መሆኑን፣

በአጠቃላይ የውሎ አበል ደንብና መመሪያን ሳይከተል ብር 8,444.55 ተከፍሎ በመገኘቱ የተከፈለው ውሎ አበል የውሎ አበል አከፋፈልን መመሪያ የተከተለ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

7. ዩኒቨርስቲው፡-
   - በትክክለኛው የሂሳብ መደብ ወጪ ተደርጎና ተመዝግቦ የነበረውን ሂሳብ የሂሳብ ማስተካከያ በሚል ትክክለኛ ባልሆነ የሂሳብ መደብ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ ሂሳቡ በትክክለኛው የሂሳብ መደብ ተመዝግቦ ቢሆን ኖሮ በድምሩ ብር 867,373.00 ከተደለደለው በጀት በላይ እንደወጣ የሚያሳይ መሆኑን፣
   - ያለሂሳብ መደባቸው በድምሩ ብር 12,480,977.25 የበጀት ዝውውር ሳይደረግ ወጪ በማድረግ ባልተፈቀደ የሂሳብ መደብ ተመዝግቦ መገኘቱን፣

   በጠቅላለው ብር 13,348,350.25 የበጀት ዝውውር ሳይደረግ ወጪ በማድረግ ባልተፈቀደ የሂሳብ መደብ ተመዝግቦ በመገኘቱ የዩኒቨርስቲው ሂሳብ እንዲዛባ አድርጓል፡፡
8. ዩኒቨርሲቲው በድምሩ የብር 4,819,559.86 ከተለያዩ ድርጅቶች ግዥ ሲፈጽም ለክፍያው በማስረጃነት መቅረብ ያለበት የሽያጭ ደረሰኝ /Cash sale invoice/ መሆን ሲገባው፣ በዱቤ የሽያጭ ደረሰኝ/Credit sale invoice/እንደ ሽያጭ ደረሰኝ በመቁጠር ሂሳቡ ተወራርዶ የተገኘ በመሆኑ የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡
9. ዩኒቨርሲቲው በድምሩ ብር 365,324.16 ለሶስት ድርጅቶች ህጋዊ የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ሳይቀርብ ክፍያ ፈጽሞ በመገኘቱ መንግሥት ከገቢ ግብር የሚያገኘውን ሂሳብ እንዲያጣ አድርጓል፡፡
10. በተለያዩ ጊዜያት ለተማሪዎች አገልግሎት የሚውሉ መስተንግዶዎችን ለማድረግ በብር 142,410.00 የተገዙ ንብረቶች ወደ ንብረት ክፍል ገቢ ስለመሆናቸው ከንብረት ክፍል ማረጋገጫ ሳይቀርብ ክፍያዎች እንደተፈፀሙ ተረጋግጧል፡፡

በዚህም የተነሳ ንብረቶቹ ለዩኒቨርስቲው አገልግሎት ስለመዋላቸው ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

11. ዩኒቨርስቲው ግዥዎችን ሲፈፅም የግዥ ደንብ፣ መመሪያውንና በአዋጁ መሠረት መፈፀሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- በጠቅላላው የብር 12,591,055.80 አገልግሎቱ የሚገኘው ከአንድ ዕጩ ተወዳዳሪ ብቻ በመሆኑ ማወዳደር የማይቻል ለመሆኑ ከሚመለከተው አካል ማረጋገጫ ሳይቀርብ ወይም በልዩ ሁኔታ ሳያስፈቅድ በቀጥታ አገልግሎቱን ከሚሰጠው ድርጅት እና ግለሰብ ግዥ የፈጸመ መሆኑን፣
- በድምሩ ብር 1,892,269.25 በግልፅ ጨረታ መግዛት ሲገባው ቆራርጦ ግዥ የፈፀመ መሆኑን፣

በአጠቃላይ ብር 14,483,325.05 በግዥ ደንብ፣ መመሪያ እና አዋጅ መሠረት ተፈፃሚ ባለመሆኑ ቁጠባን የአፈፃፀም ብቃትንና ውጤታማነትን ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

12. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 100 ንዑስ አንቀጽ 3 ለትርፍ የቆመ ድርጅት ካልሆነ በስተቀር ክልሎች በፌዴራሉ መንግስት ንብረት ላይ፣ የፌዴራሉ መንግስትም በክልሎች ንብረት ላይ ግብር ወይም ቀረጥ የማስከፈል ስልጣን አይኖራቸውም በማለት የተደነገገ እና ዩኒቨርሲቲው መንግስት የተማረ የሰው ኃይል ለማፍራትና ማህረሰብ አቀፍ ችግሮችን ለመፍታት የሚገለገልበትን መሬት በነፃ የተሰጠ መሆኑ እየታወቀ ለወልድያ ከተማ አስተዳደር ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ያለአግባብ የይዞታ /የቦታ/ኪራይ በሚል በድምሩ ብር 2,981,759.91 ክፍያ በመፈፀሙ ህገ መንግሥቱ ካስቀመጠው በተቃራኒ መሆኑን እና በዚህ መጠን የዩኒቨርስቲው ወጪ አለአግባብ እንዲወጣ አድርጓል፡፡

13. ዩኒቨርሲቲው ከሌላ ቦታ እንግዶችን ለስራ ወደ ዩኒቨርሲቲው ሲመጡ ተቀብሎ የሚያሳርፍበት የእንግዳ ማረፊያ (Guest House) በጀት ተመድቦለት በግቢው ውስጥ ያስገነባ መሆኑ እየታወቀ ብር 162,650.00 ወጪ ሊያደርገው የማይገባ ገንዘብ ወጪ አድርጎ ለግራንድ ኢንተለጀንስ ኢንተርፕራይዝ ክፍያ የፈጸመ በመሆኑ አለአግባብ የዩኒቨርስቲው ወጪ እንዲወጣ አድርጓል፡፡

14. ዩኒቨርሲቲው የበጀት ዓመቱን ክፍያ በበጀት ዓመቱ ውስጥ መክፈልና ማወራረድ ሲገባው በድምሩ ብር 3,143,569.76 በ2010 በጀት ዓመት መክፈል እና መወራረድ የሚገባው በ2011 በጀት ዓመት ላይ ክፍያ የተፈፀመና የተወራረደ መሆኑን ተረጋግጧል፡፡ በዚህ ምክንያት የሂሳብ ሪፖርቱ ላይ የተመለከተው ትክክለኛውን የበጀት ዓመቱን ወጪዎች እንዳያመለክት አድርጓል፡፡
15. የዩኒቨርሲቲው የግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤትና የብሄራዊ መሃንዲስ በተዘጋጁ አስር የመመዘኛ መስፈርቶች በማወዳደር በቀን 29/05/09 ህንጻ ተቋራጭ ዳንኤል ፀጋዬ በአጠቃላይ ነጥብ በብልጫ የለየ ቢሆንም የመንግስት የግዥ መመሪያን ባልተከተለ እና ከግዥ እና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት እውቅና ውጭ ከመሆኑ በተጨማሪ በቀን 07/06/09 የግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ባለሙያዎች ባልተሳተፉበትና አስተያየት ባልሰጡበት ሁኔታ በዩኒቨርሲቲው የሥራ አመራር ውሳኔ ያለ ምንም በቂና አሳማኝ ምክንያት በተቀመጡ መስፈርቶች መሰረት አሸናፊ ተደርጎ የተመረጠውን ህንጻ ተቋራጭ ዳንኤል ፀጋዬን ውድቅ በማድረግ የግንባታ ስራው 2ኛ ለወጣው ህንጻ ተቋራጭ ለጌትነት ተስፋዬ ህ/ሥ/ተቋራጭ በመስጠት ከዩኒቨርሲቲ ጋር የምግብ ማብሰያ ግንባታ ለመስራት በብር 169,801,697.35 ቫትን ጨምሮ ውለታ እንዲገባ የተደረገ በመሆኑ ፍታዊ ውድድር እንዳይኖር ከማድረጉም ባሻገር አፈጻጸሙ ለብልሹ አሰራር በር እንዲከፈት አድርጓል፡፡
16. የዩኒቨርሲቲው የግንባታ ፕሮጀክቶች በዋናው ግቢ እና መርሳ ሳይት የተጀመረበት እና የሚጠናቀቅበት ጊዜ የግንባታ የውል አፈጻጸም የተፈፀመ ሲሆን ነገር ግን መጠናቀቅ ከሚገባው ከውሉ በላይ በመሆኑ በድምሩ ብር 5,146,318.44 የጉዳት ካሳ ቅጣት ያልሰበሰበ በመሆኑ ለመንግስት ገቢ መሆን የነበረበት እንዳይገባ ከማድረጉም ባሻገር አፈጻጸሙ ለብልሹ አሰራር በር እንዲከፈት አድርጓል፡፡

<u>የተሰብሳቢ ሂሳብ፣</u>

17. ዩኒቨርስቲው በ2011 በበጀት ዓመት መጨረሻ ከሚታይ ተሰብሳቢ ሂሳብ ውስጥ በድምሩ ብር 56,287,404.25 ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ድረስ መወራረድ ሲገባ ያልተወራረደ ተሰብሳቢ ሂሳብ መኖሩን፣

<u>የተከፋይ ሂሳብ፣</u>

18.ዩኒቨርሲቲው በገባው ግዴታ መሰረት በወቅቱ መክፈል ሲገባው ከመደበኛ በጀት በድምሩ ብር 22,843,545.14 በተከፋይ ተይዞ የሚታይ መሆኑን፣

በጀት፣

19.ዩኒቨርስቲው ከመደበኛ በጀት በድምሩ ብር 26,650,487.27 ለየሂሳብ መደቦቹ ከተደለደለው(ከተፈቀደው) በጀት በላይ ተጠቅሞ በመገኘቱ የወጪ ሂሳብ በጀቱ በዕቅዱ መሠረት አለመፈፀሙ የዩኒቨርስቲውን ዓመታዊ የሥራ ውጤት ዝቅ ያደርገዋል፡፡

ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 19 በተገለጹት ጉልህና መሠረታዊ ልዩነቶች የተነሳ በእኛ አስተያየት የዩኒቨርስቲውን የሂሳብ መግለጫዎች ሰኔ 30 ቀን 2011 ዓ.ም የተመለከተውን የፋይናንስ አቋም እና የበጀት ዓመቱን የሥራ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በአጥጋቢ ሁኔታ አያሳዩም፡፡

ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች፣

ምንም እንኳን በሰጠነው አስተያየት ላይ ለውጥ ባያስከትሉም ቀጥሎ የተመለከቱት ጉዳዮች ትኩረት ሊደረግባቸው፣ እርምጃ ሊወሰድባቸው እና ለወደፊቱም ጥንቃቄ ሊደረግባቸው ይገባል፡፡

- ዩኒቨርሲቲው ከክረምት እና ከማታ ተማሪዎች በድምሩ ብር 18,470,987.09 ገቢ የሰበሰበ እና በጥቅሉ ባንክ ገቢ የተደረገ ቢሆንም በያንዳንዱ ተማሪ ስም በመሂ-1 ተቆርጦ በሞዴል-64 መጠቃለል ሲገባው በመሂ-1 ተጠቃልሎ ምዝገባ የተከናወነ መሆኑን፣
- የሚኒስትሮች ምክር ቤት ግንቦት 25 ቀን 2009 ዓ.ም በበጀት ላይ የወጪ ቅነሳ ቁጥር 17 መሠረት ድጋፍና ስጦታን ባለበጀት መ/ቤቶች/ ከዩኒቨርስቲዎች ከክረምት ተከታታይ ተማሪዎች እና በዩኒቨርስቲዎች ከሚማሩ አካል ጉዳተኞች በስተቀር ለማንኛውም ድርጅት ሆነ ግለሰብ የገንዘብ ድጋፍ ወይም ስጦታ መስጠት እንደማይቻል ቢገለጽም ዩኒቨርሲቲው ከህግና ደንብ ወጪ በድምሩ ብር 71,467.50 ለሁለት የዩኒቨርሲቲው ኃላፊዎች የስጦታ ዕቃ ግዥ ያለ አግባብ ፈጽሞ የተገኘ መሆኑን፣

- ዩኒቨርሲቲው ብር 121,968.00 ወጪው ከፌደራል መንግስት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት ውጭ ባልተገባ ሁኔታ በ6116 የሂሳብ መደብ ተመዝግቦ ሪፖርት መደረግ ሲገባው፣ በ1443 ተከፍሎ ምዝገባ የተከናወነ መሆኑን፣
- የዩኒቨርሲቲው የበጀት አስተዳደር ከሐምሌ/2010 እስከ ሰኔ 30/2011 የተስተካከለ በጀት በየሂሳብ አርዕሶቹ በትክክለኛ ከወጣው ወጪ ጋር ሲነጻጸር ከ10% በላይ ከመደበኛ በጀት ብር 32,256,179.73 እና ከካፒታል በድምሩ ብር 21,368,518.15 በጠቅላላ ድምር 53,624,697.88 ሥራ ላይ ያልዋለ መሆኑን፣
- የዩኒቨርሲቲው የውስጥ ኦዲት የገንዘብ ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ባወጣው ሪፖርት ማቅረቢያ የጊዜ ሰሌዳ ማለትም የመጀመሪያው ሩብ አመት ሪፖርት እስከ ጥቅምት 30 ድረስ፣ የሁለተኛው ሩብ አመት እስከ ጥር 30 ድረስ፣ የሶስተኛው ሩብ አመት ሪፖርት እስከ ሚያዚያ 30 እንዲሁም የአራተኛ ሩብ አመት ሪፖርት እስከ ነሃሴ 15 ድረስ መቅረብ ሲገባው የመጀመሪያው ሩብ አመት ሪፖርት በቀን 24/04/2011፣ የሁለተኛው ሩብ አመት ሪፖርት በቀን 13/06/2011፣ የሶስተኛው ሩብ አመት በቀን 23/09/2011 የቀረበ መሆኑ እንዲሁም የአራተኛ ሩብ አመት እስከ 17/02/12 ድረስ ሪፖርት ያልተደረገ መሆኑን፣

<u>ሌሎች ጉዳዮች፣</u>

- የዩንቨርሲቲው የንብረት አያያዝ፣ አመዘጋገብ፣ አጠባበቅ፣ አወጋገድ እንዲሁም የተሽከርካሪዎች ማህደር አያያዝ በተመለከተ:-
- Food waste drayer machine ብዛት 2 በብር 31,000,000.00 ተገዝቶ የመጣ (የተረፈ ምርት ማቀነባበሪያ ማሽን) ከ1 ዓመት በላይ ያለ አገልግሎት የተቀመጠ መሆኑን፣
- በእርዳታ መልክ የገቡ ብዛት ያላቸው የህክምና እቃዎች (ሙሉ ኮንቴነር)፣ በግዥ የገቡ በቁጥር 20 የሚሆኑ የላይብረሪ ሸልፍ፣ የምግብ ቤት ዕቃዎች drough boulder፣ የተለያዩ የሙዚቃ መሳሪያዎች፣ ላደር ሜል ድስትሪቢዩሽን ቦርድ፣ የላውንደሪ ማሽን፣ ብዛታችው 15 የሆኑ የምግብ ቤት ዕቃዎች (የሊጥ ማቡኪያ) ማሽን፣ ከትምህርት ሚኒስቴር የመጣ የስጋ ፍሪጅ፣ ብዛታቸው 13 የሆኑ ከትምህርት ሚኒስቴር የተሰጡ የዉሀ

ሲንኮች፤ብዛት ያላቸው ፋይል ካቢኔቶች፣ ብዛታቸው 5 የሆኑ ከትምህርት ሚኒስቴር የተሰጡ የውሀ ማፍያ ማሽን፣ ትልቅ የሆነ የውሃ ማሞቂያ (ቦይለር)፣ ከሁለት ዓመት በላይ ያለአገልግሎት የተቀመጡ መሆኑን፣

- ብዛት ያላቸው ንብረቶች አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች የመኪና ጎማዎች፣ ብዛት ያላቸዉ ወንበሮች፣ ጠረጴዛዎች፣ ፋይል ካቢኔቶችና የበር ስብርባሪዎች፤ የተበላሹ የአገር ዉስጥ ፋዝ፣ ምስር ክክ እና አተር ክክ፤ አገልግሎት የማይሰጡ የዳቦ ካሳዎች፣ ስቶቭ፣ መወገድ የሚገባቸው ንብረቶች ያልተወገዱ መሆኑን፣
- በጠቅላላ በብር 4,096,753.13 የተገዙ ፍራሽ ትራስ እና ተደራራቢ አልጋ ያለአገልግሎት የተቀመጡ መሆኑን እና ፍራሾችና ትራሶቹ አይጥ እየተበሉ መሆናቸው፣
- ብዛት ያላቸው አገልግሎታቸዉ ያለፈባቸዉ መድሃኒቶች በዲስፔንሰሪ ስቶር እና የህክምና እቃዎች ስቶር ዉስጥ ተሰብስበዉ አንድ ቦታ ተቀምጠው መወገድ ሲገባቸዉ አቀማመጣቸውም የተለያየ ቦታ ከመሆኑ በተጨማሪ መወገድ ሲገባቸው ሳይወገዱ መገኘታቸው፣ በተጨማሪም አንቀጽ16(1) መድሀኒቶች ካላቸው ልዩ ተፈጥሮ የተነሳ ቢበዛ በየ3 ወሩ መቆጠር እንዳለባቸው ቢያመለክትም ዩኒቨርስቲው በ2011 በጀት ዓመት መጨረሻ የመድኃኒት ቆጠራ ያልተደረገ መሆኑን፣

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት